# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 291 ህዳር 27 2006 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

> ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በችግር ላይ የሚገኙ ወገኖቻችንን ከመርዳት ጎን ዓይኖቻችንን ከወያኔ እንዳንነቅል በአጽንዖት ያሳስባል። ወያኔ ከሥልጣን ሳይወገድ ችግሮቻችንን መፍታት አንችልም። የኢትዮጵያዊያን ችግሮች ለወያኔ የገቢ ምንጮች ናቸና ወያኔ እስካለ ድረስ ችግሮችን መፍጠሩና ማስፋፋቱ አይቀርም።
>
> ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የወያኔ አገዛዝ በመልዕክተኞቹ በኩል ላቀረበው የ"እንደራደር" ጥያቄ ከግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ ምላሽ

ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ የገነባዉ ሥርዓት በከፍተኛ ችግሮች የተወጠረ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የመሪው ሞት በወያኔ መሀል ያስከተለው ቀውስ፤ የሕዝብ ሁለገብ ትግል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበት መሄድ የፈጠረበት ስጋት እና ምርጫ በደረሰ ቁጥር የሚደርስበት ጭንቀት መጨመር ተደማምረው ውጥረቱን ወደ ከፍተኛ ደረጃ እያደረሱት መሆኑን የሚያሳዩ በቂ ምልክቶች አሉ። የእስካሁኑ ተሞክሮዓችን እንደሚያሳየው ወያኔ ውጥረት ሲበዛበትና መዉጪያና መግቢያዉ ሲጠፋዉ፣ ተቃዋሚ ድርጅቶችን "እንወያይ፣ እንደራደር" በማለት ለውጥረት ማስተንፈሻ ጊዜ የሚገዛ መሆኑን ነው። ሰሞኑን በወያኔ አገዛዝ መልዕክተኞች በኩል የደረሰንን "የእንደራደር" ጥያቄ ንቅናቄያችን በዋናነት ያየው ወያኔ እንደለመደው ድርድርን ለውጥረት ማስተንፈሻነት ለመጠቀም እየሞከረ መሆኑን ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመኘው ዲሞክራሲያዊ ለውጥ በሰላማዊ መንገድ በሚደረግ ትግልና በጠረጴዛ ዙሪያ በሚደረጉ ዉይይቶች ቢመጣ የግንቦት 7 ምርጫ መሆኑን ንቅናቄያችን በተደጋጋሚ ግልጽ አድርጓል። ግንቦት 7ን ሁለገብ ትግል ውስጥ እንዲገባ ያስገደደው የወያኔ እምቢተኝነትና እብሪት ብቻ ነው።

የግንቦት 7 ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሰሞኑ የወያኔ የእንደራደር መልዕክት እንደደረሰው በጉዳዩ ዙሪያ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ይህ ጉዳይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ባጠቃላይ እንጂ ግንቦት 7ን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ እንዳልሆነ ከድምዳሜ ላይ ደርሷል። ይህ ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ከሚያደርገው ትግልና እየከፈለ ካለው ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ኔልሰን ማንዴላ በሕይወት ቢለዩንም በመንፈስ አብረውን ይቆያሉ

የግንቦት 7 መግለጫ

በአፓርታይድ የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ብቻ ሳይሆን በዩ. ኤስ. አሜሪካ ጭምር ሽብርተኛ ተብለው ሲሳደዱ፣ ሲታሰሩና ሲሰቃዩ የሕይወታቸውን አጋማሽ የጨረሱ፤ በመሣሪያ የታገዘ አመጽንና ሕዝባዊ እምቢተኝነትን አጣምሮ የያዘ ሁለ-ገብ ትግል በመምራት ለአፓርታይድ አገዛዝ ማብቃት ከፍተኛ ድርሻ ያለው የትግል አስተዋጽዖ ያደረጉ፤ ለመላው ዓለም የነፃነት ታጋዮች አርአያ የሆኑት ኔልሰን ማንዴላ አረፉ።

ኔልሰን ማንዴላ የነፃነት ትግልን በግንባር በመሰለፍ መርተዋል። ኢትዮጵያ ድረስ በመምጣት ወታደራዊ ሥልጠና ወስደው ዘረኛዉን የፕሪቶሪያ አገዛዝ በመሣሪያ ታግለዋል። የእሳቸው ጠመንጃ ማንሳት ለበርካታ ወጣት ታጋዮች አርዓያ ሆኗል። እስር ቤት በቆዩባቸው 27 ዓመታት ደግሞ የድርጅታቸውንና የትግሉን አመራሩ ለጓዶቻቸው በመተው እርሳቸው ለነፃነትና ለእኩልነት በመታሰርና ስቃይን በመቀበል ትግሉን መርተዋል። በዚህም ምክንያት በትግል ሜዳም በእስር ቤትም መሪ እንደሆኑ የዘለቁ ታላቅ አፍሪቃዊ ናቸው።

ከነፃነት በኋላ ደግሞ ኔልሰን ማንዴላ በሕዝብ ነፃ ፈቃድ የተመረጡ የአዲሲቷ ደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያ ፕሬዚዳንትነት ሆነዋል። በየምርጫው ተወዳድሬ አሸንፌ በፕሬዚዳንትነት ልቀጥል ሳይሉ በአፍሪቃ ባልተለመደ ሁኔታም አንድ ዙር ብቻ አገልግለው ደግመው ላለመወዳደር ወስነው በጊዜ ሥልጣናቸውን በመልቀቅ መርተዋል። በመሆኑም ኔልሰን ማንዴላ ሥልጣን ላይ ሆነውም ሥልጣን ለቅቀውም መሪ መሆን የቻሉ ድንቅ አፍሪቃዊ ናቸው።

ኔልሰን ማንዴላ ታላቅ የነፃነት አርበኛ፣ ታላቅ የለውጥ አራማጅ፣ ታላቅ መምህር እና ታላቅ የእርቅ ሰው ነበሩ። ዛሬ ዓለም እኚህን ታላቅ አፍሪቃዊ አጣች።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በኔልሰን ማንዴላ ሕልፈት የተሰማውን ጥልቅ ሐዘን ይገልፃል። ከእንግዲህ ማንዴላን የምናስባቸው ከእሳቸው ተሞክሮ የምንማረው ሲኖር ነው። በዘረኝነት እየተጠቃን ላለነው ኢትዮጵያዊያን የማንዴላ ትምህርት ሕያው ሊሆን ይገባል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ዘረኝነትን በጽናት የመታገል ሆኖም ግን ይቅር ባይ የመሆንን እሴቶች ተግባራዊ በማድረግ ማንዴላ በሕይወት ቢለዩንም በመንፈስ ሁሌም አብረውን እንዲኖሩ እናድርግ ይላል።

**የግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነት**

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## የወያኔ አገዛዝ ከግቦት ሰባት የፍትህ የነጻነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ጋር ልደራደር ብሎ መጠየቁ ተሰማ

ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዴሞክረሲ ንቅናቄ በፋሽስት ወያኔ ወዳጆች አማካኝነት ሰሞኑን የእንደራደር ጥያቄ ከፋሽስት ወያኔ እንደቀረበለት ገለጸ። የእንደራደር ጥያቄውን አስመልክቶም የአቋም መግጫ አውጥቷል።

የእስካሁኑ ተሞክሮዓችን እንደሚያሳየው ይላል ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የእስካሁኑ ተሞክሮዓችን እንደሚያሳየው ወያኔ ውጥረት ሲበዛበትና መዉጪያና መግቢያዉ ሲጠፋዉ፣ ተቃዋሚ ድርጅቶችን "እንወያይ፣ እንደራደር" በማለት ለውጥረት ማስተንፈሻ ጊዜ የሚገዛ መሆኑን ነው። ሰሞኑን በወያኔ አገዛዝ መልዕክተኞች በኩል የደረሰንን "የእንደራደር" ጥያቄ ንቅናቄያችን በዋናነት ያየው ወያኔ እንደለመደው ድርድርን ለውጥረት ማስተንፈሻነት ለመጠቀም እየሞከረ መሆኑን ነው ብሏል። ከዚህም በላይ የድርድር ጥያቄው ለኛ ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለሌሎችም የፖለቲካ ፓርቲዎችም መቅረብ እንዳለበት ግንቦት 7 ጠቅሶ ዓላማውም የኢትዮጵያን ሕዝብ የስልጣን ባለቤት የሚያደርግ የፖለቲካ ስርአት ግንባታ ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል ብሏል።

ከዚህ በተጨማሪም ግንቦት 7 ድርድሩ የጭንቅ ጊዜ መግዣ እንዳልሆነ ለማሳየት ድርድሩ የእውነት መሆኑን ሊያረጋግጡ የሚችሉ የፖለቲካ እስረኞችንና ጋዜጠኞችን ከእስር መፍታት፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ ወያኔ እየወሰደ ያለውን ወከባና ሰብአዊ መብት ረገጣ ማቆምና መብተቸውን ማክበር፣ ከዚህ በፊት የተወሰዱ ከፖለቲካ ጋር የተያያዙ ሁሉም አይነት ፍትህ ተብየ ውሳኔዎች መሻርና አሁን በሂደት ላይ ያሉትን ክሶችም መቋረጥ፣ ሕዝብን ለማሸበርና በፍርሃት ቆፈን ስር ለማስቀመጥ ብቻ የወጡ አፋኝ ህጎችን መሻርና ማንኛውም ድርድር ገለልተኛ የሆኑ ሶስተኛ ወገኖች ባሉበት፤ የድርድሩ ሂደት በምስልና በድምጽ ተቀርጾ በገለልተኛ ወገኖች እጅ ብቻ የሚቀመጥ፣ የድርድሩ ቦታም የተደራዳሪ ወገኖች በጋራ በሚስማሙበት ቦታ መሆኑን መቀበልና ይህንንም በግልጽ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማሳወቅን የመሳሰሉትን መተማመኛዎች ፋሽስት ወያኔ መውሰድ አለበት ብሏል። በ2002 ዓመተ ምህረት በተደረገው የይስሙላ ምርጫ ደግሞ በሃገር ውስጥ የሚንቀሳቀሳቀሱ ፓርቲዎች ጋር ፍትሃዊ ያልሆነ ድርድር በማድረግ እና ከፍተኛ የምርጫ ማጭበርበር በመፈጸም ሙሉ በሙሉ የፓርላማውን መቀመጫ የወያኔ አገዛዝ ጭፍራዎች መቆጣጠራቸው ይታወቃል፡፡

## የደቡብ አፍሪካው የነጻነት ታጋይ እና የቀድሞ ፕሬዝዳንት ኔልሰን ማንዴላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ

የደቡብ አፍሪካን ዘረኛ ስርዐት ታግለዉ ያንበረከኩትና አገሩቱን ወደ እዉነተኛ ዲሞክራሲ ስርዐት የመሯት በሰላም ፈላጊነታቸዉ፤ በአመራር ብስለታቸዉና በአርቆ አስተዋይነታቸዉ ወደር የማይገኝላቸዉ የአለማችን ታላቅ ሰዉ ኔልሰን ማንዴላ በተወለዱ በ95 አመታቸዉ ትናንት ህዳር 26 ቀን 2006 ዓም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የትግል አቻቸዉና የአሁኑ የደቡብ አፍሪካው ፕሬዝዳንት ጃኮብ ዙማ ዛሬ ደቡብ አፍሪካ እጅግ በጣም ትልቅ ሰው አጥታለች በማለት የጀግናዉን ሞት ለአለም ህዝብ ተናግረዋል።

እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1918 ዓመተ ምህረት ዞሳ በምትባለው የደቡብ አፍሪካ ከተማ የተወለዱት የነጻነት ታጋዩ ኔልሰን ማንዴላ በለጋ የወጣትነት እድሜው ነበር የነጻነት ትግላቸዉን የጀመሩት፡፡ ኔልሰን ማንዴላ በወቅቱ በደቡብ አፍሪካ በጥቁር እና ነጭ መካከል ሰፍኖ የነበረውን አአድሎአዊና ዘረኛ አገዛዝ በመቃዎም በሃገሪቱ ስልጣን ላይ የነበረውን ዘረኛ የአፓርታይድ አገዛዝ ታግለዋል፡፡ ማንዴላ ወይንም በሃገሩ ሰዎች አጠራር ማዲባ የአፓርታይድን አገዛዝ በመቃወማቸዉ እና በሃገራቸዉ ነፃነት ለማምጣት፣ ፍትህ እና እኩልነት ለማስፈን እና ድህነትን ለመቅረፍ በመታገላቸዉ ምክንያት ለ27 ዓመታት በሮቢን ደሴት በእስር ላይ ቆይተዋል፡፡ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል መጠናከር ወያኔን የቀን ቅዠት ውስጥ እንደከተተው ታወቀ

በወያኔ ጦር ውስጥ ተፈጥሮ የነበረው አለመተማመንና ክፍፍል እጅግ በጣም ከፍ ያለ ደረጃ ላይ መድረሱን ያገኘናቸው መረጃዎች ያረጋገጡ ሲሆን ከግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል መጠናከርና እያደር ስሙ ገናና እየሆነ መምጣት ጋር ተያይዞም የወያኔ ቁንጮዎች እንቅልፍ እያጡ መሆናቸው ታወቋል።

ከትምህርትና ከበቂ የአገልግሎት ዘመን ውጭ በጎጥና ዝምድና ሰበብ ያገኙትን ስልጣን መከታ በማድረግ ባጋጣሚ በእጃቸው የገባውን ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የችግሮቻችን የመፍትሔ ቁልፍ - ወያኔን አስወግዶ ፍትህን ማስፈን

አሁንም በሳውዲ አረቢያ እና አካባቢው አገሮች የሚገኙ ወገኖቻችን የድረሱን ጥሪዎች እያሰሙ ነው። የወገኖቻችን ዋይታና ሰቆቃ አልበረደም። ዛሬም እህቶቻን እየተደፈሩ፣ እየተዋረዱ፣ እየተገደሉ ናቸው። በጥጋብ አገር ውስጥ ሆነው ኢትዮጵያዊያን ሕፃናት በረሀብና በጥም እየሞቱ ነው። በርካታ ኢትዮጵያዊያን ለከፋ የአዕምሮ ህመም እየተዳረጉ ነው።

በተለያዩ የዓለም አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ ወገኖቻቸውን ሕመም እየታመሙ፤ ስቃያቸውን እየተሰቃዩ ይገኛሉ። አስቸኳይ እርዳታ ለማድረስም አቅማቸው የቻለውን ሁሉ ለማድረግ በመረባረብ ላይ ናቸው።

ባለፉት ጥቂት ሣምንታት ኢትዮጵያዊያን ባደረጓቸው ብርቱ ጥረቶች ጥቂት አበረታች ውጤቶች ተገኝተዋል። ከደረሰባቸው የመብት ረገጣ ጋር ፈጽሞ ተመጣጣኝ ባይሆንም ቢቢሲን ጨምሮ አንዳንድ የዓለም ዓቀፍ የዜና አውታሮች በወገኖቻችን ላይ ስለሚደርሰው በደል እንዲዘግቡ ማድረግ ተችሏል። እስካሁን ምን ያህል ወገኖቻችን እድሉን እንዳገኙ ማረጋገጥ ባይቻልም የሳውዲ መንግሥት ሙሉ የትራንስፓርት ወጪ ችሎ ወገኖቻችን ማጓጓዝ ጀምሯል። ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች ለኢትዮጵያዊያን መብት መከራከር ጀምረዋል።

በአንፃሩ ግን አሁንም ሕሊናን የሚረብሹ ነገሮች እየተሰሙ ነው።

1. ከሳውዲ እየታፈሱ የመን ድንበር ላይ የተጣሉ፤ የደረሱበት የማይታወቁ ኢትዮጵያን ቁጥር በየእለቱ እየጨመረ ነው። እነዚህ ወገኖቻችን በየመን በረሀ ላይ የሚደርስባቸው ሰቆቃ ሳውዲ ውስጥ ከነበረው የባሰ ነው።
2. አሁንም በሳውዲ ተደብቀው የሚገኙ፤ "እጃቸውን ለመንግሥት ሰጥተው" እንደ ወንጀለኛ በእስር ቤቶች የሚማቅቁ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን አሉ። እነዚህ ወገኖቻችን ያሉበት ሁኔታ ሕሊና ሊሸከመው ከሚችል በላይ ነው።

ከዚህ ሁሉ በላይ ኢትዮጵያዊያንን እየረበሸ ያለው የወያኔ ባህርይ ነው።

ወያኔ በእንዲህ ዓይነት የመከራ ወቅትም በወገኖቻችን ላይ ዘርፈ ብዙ ንግድ እያጧጧፈ ነው። በሳውዲ አረቢያ መንግሥት ወጪ የተመለሰሉትን ወገኖቻችን ለምርጫ ቅሰቀሳ ፕሮፖጋንዳ ሥራ እየተጠቀሙባቸው መሆኑ ሳያንስ ለእለት ጉርስ የሚሰጣቸው የእርዳታ ገንዘብ በወያኔ እየተዘረፉ ነው። ገንዘብ ባለበት ሁሉ ወያኔ አለ። ወያኔ ለተመላሽ ስደተኞች የእለት ጉርስ የተሰጠውንም እርዳታ እየቀማ የሚበላ እኩይ ኃይል ነው።

ድሆች ኢትዮጵያዊያን ወደ አረብ አገራት ሲሰደዱ ለወያኔ ድርጅቶች ገንዘብ ከፍለው ነው። እዚያ በነበሩበት ጊዜም ለወያኔ ገንዘብ እንዲከፍሉ ይደረግ ነበር። በግፍ ተፈናቅለው፤ ሀብታቸው ተዘርፎ ባዶ እጃቸውን ሲመለሱም ለወያኔ የእርዳታ ገንዘብ መለመኛ ሆነዋል። ወያኔ በድሆች ኢትዮጵያዊያን ድህነት የሚከብር በታሪካችን ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ስግብግብ ነው። ወያኔ ኢትዮጵያዊያን ፈጽሞ ሊጠየፉት የሚገባ ነው ስብስብ ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በችግር ላይ የሚገኙ ወገኖቻችንን ከመርዳት ጎን ዓይኖቻችንን ከወያኔ እንዳንነቅል በአጽንዖት ያሳስባል። ወያኔ ከሥልጣን ሳይወገድ ችግሮቻችንን መፍታት አንችልም። የኢትዮጵያዊያን ችግሮች ለወያኔ የገቢ ምንጮች ናቸና ወያኔ እስካለ ድረስ ችግሮችን መፍጠሩና ማስፋፋቱ አይቀርም።

የኛ የኢትዮጵያዊያን ችግሮች የመፍትሔ ቁልፍ ያለው ወያኔን በማስወገድ ፍትሀዊ አመራር ማስፈን ላይ በመሆኑ የጋራ ትኩረታችን እዚያ ላይ እንዲሆን ግንቦት 7 ያሳስባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

---

## የወያኔ አገዛዝ በመልዕክተኞቹ በኩል ላቀረበው የ"እንደራደር" ጥያቄ ከግንቦት 7 . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

መስዕዋትነት ጋር በቀጥታ ግንኙነት አለው። በመሆኑም፤ ለቀረበልን ጥያቄ ግልጽ መልስና፤ ድርድር ስለሚባለው ጉዳይም ያለንን አቋም ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከተው የኢትዮጵያ ሕዝብና የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ለማቅረብ የሚያስችል ተጨማሪ አጋጣሚ አድርገን ወስደነዋል። በዚህም መሠረት ለቀረበልን ጥያቄ የሰጠነዉን መልስና አቋማችንን በድርጅታችን ድረ ገጽ ላይና በሌሎች መገናኛ ብዙሀን በኩል በይፋ ለመግለጽ ወስነናል።

### በድርድር ስለሚመጣ ለውጥ ያለን የመርህ አመለካከት

ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽ እንዳደረግነው ድርጅታችን ከምሥረታው ጀምሮ የትግል ስልቱን ሲወስን እምነቱ አድርጎ የተነሳው ዴሞክራሲያዊ ለውጥ በሀገራችን በሰላማዊ መንገድና በድርድር ቢመጣ በእጅጉ የሚፈልገውና የሚመኘው መሆኑን ነው:: ድርጅታችንን ወደ ሁለንተናዊ ትግል የገፋው በመግቢያው ላይ እንደገለጽነው የወያኔ እብሪት ብቻ ነው:: የቀረበልን ምርጫ በባርነትና በውርደት መኖር ወይም ለነፃነት እየታገልን መሞት ቢሆን ኖሮ ንቅናቄያችን የሚመረጠው ምን ግዜም ለነፃነትና ለአገር አንድነት ታግሎ በክብር መሞት መሆኑን በተደጋጋሚ ለሕዝብ ግልጽ አድርገናል። ይህ የማይናወጥ አቋማችን ደግሞ ለይምሰል የተቀመጠ አቋም ሳይሆን ከልባችን የምናምንበትና ኢትዮጵያን ጨምሮ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ አባላቶቻችንን ያሰባሰብንበት አቋም ነው። ዛሬ በትግሉ ግንባር የምንንቀሳቀሰውና ወደ ግባችን የሚወስደንን ተጨባጭ እርምጃዎች እየወሰድን ያለነውም በዚሁ አቋማችን ዙሪያ ነዉ።

ይህ አቋማችንና እምነታችን በአንድ ላይ ጎን ለጎን የሚሄዱ ሁለት መርሆችን አጣምሮ የያዘ ነዉ። አንደኛው፣ ሂደትን በሚመለከት ሁሌም ለድርድር ክፍት መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ፣ ይህ የድርድር ሂደት እንዲያው ለለበጣ የሚደረግ ሳይሆን ወደሚፈለገው ነጻነት በአነስተኛ መስዕዋትነት ሊያደርስ ይችል ከሆነ በሩን ላለመዝጋት እንጂ፣ በምንም አይነት ዋና ውጤቱን፤ ማለትም ኢትዮጵያን እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሀገር ማድረግን፤ የሚቀይር ወይንም ከዚያ ያነሰ ውጤትን ለመቀበል መፍቀድን ፈጽሞ የማያመለክት መሆኑን ነው::

በእኛ በኩል ድርድሩን አስፈላጊና ጠቃሚ የሚያደርጉት መነሻ የፖለቲካ እሳቤዎችም ከእነኝሁ ሁለት መንታ ገጽታዎች የሚመነጩ ናቸው:: በድርድር ለሚገኝ ፍትሀዊና እውነተኛ ውጤት ክፍት መሆናችንን ሁሌም እናሳያለን፤ ነገር ግን ይህን የምናደርገው የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት የተረጋገጠባትን ኢትዮጵያን እውን ማድረግ የሚጠይቀውን ማንኛውንም መስዋዕትነት መክፈል አለበት የሚለውን መሠረታዊ የአካሄድ መርህ በመመርኮዝ እንጂ መርሀችንን ለድርድር ለማቅረብ እንዳልሆነ በግልጽ መታወቅ ይኖርበታል::

ስለዚህም:

ሀ)የድርድሩ ውጤት የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ያረጋገጠ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በአስቸኳይ እውን ማድረግ መሆን ይኖርበታል:: ይህ ዋናው ግብ ሆኖ ከዚህ በመለስ የሚኖሩ በሂደት የሚገኙ አነስተኛ ግቦች ሊኖሩ ይችላሉ (ለምሳሌ የፖለቲካ እስረኞች ማስፈታት…ወዘተ):: ሆኖም በምንም አይነት ለእነኝህ መለስተኛ ግቦች ተብሎ ዋናውን ግብ የሚያሳጣ ወይንም ጊዜውን ያላግባብ የሚያስረዝም ድርድር፣ ድርድር ነው ብሎ ድርጅታችን አይቀበልም። ስለዚህም ዋናው የድርጅታችን ዓላማና ግብ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ፣ በፍጹም ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም:: በሥልጣን ላይ ባለው ኃይል በኩል ወደዚህ ግብ ለመድረስ ቁርጠኝነቱ በሌለበት ሁኔታ በሚደረግ ማንኛውም አይነት ድርድር ውስጥ ግንቦት 7 አይሳተፍም::

ለ) በግንቦት 7 እምነት ማንኛውም ድርድር ወያኔ ከግንቦት 7 ጋር በተናጠል የሚያደረገው ሳይሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች ያካተተ መሆን ይኖርበታል:: ድርጅቶችን በተናጠል እየለያዩ "እንደራደር" ማለት በራሱ ጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ስሌትን የያዘ እሳቤ እንጂ፣ በዘላቂነት አገሪቱን እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ አገር ለማድረግ መፈለግን አያመለክትም:: ለአንድ ድርጅት ለብቻው የሚመጣ ወይም የሚጠቅም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የለም:: ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመፍጠር ፍላጎት ያለው ድርድር በአገሪቱ ያሉትን የተለያዩ የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ኃይሎችን ያካተተና ያመኑበት መሆን ይኖርበታል:: የሚደረገው ድርድርም ማን በስልጣን ላይ ይውጣ ወይንም የፖለቲካ ስልጣንን ባሉት ኃይሎች መሀከል እንዴት እናከፋፍለው የሚል የስልጣን ቅርምት ድርድር ሳይሆን፤ ሕጋዊና የሕዝቡን የሥልጣን ሉዓላዊነት ባረጋገጠ ሁኔታ የፖለቲካ ስልጣን እንዴት እንደሚያዝ ፍትሀዊ የሆነ ሂደትን ለማስጀመር የሚደረግ ድርድር መሆን አለበት::

ሐ) ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ይህ ጉዳይ የሚመለከተው አንድን ድርጅት ወይንም የፖለቲካ ድርጅቶችን ብቻ ሳይሆን መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ነው:: ይህ እስከሆነ ድረስ እንዲህ አይነት ድርድር ከሕዝቡ በተደበቀ ሁኔታ በሚስጥር የሚካሄድበት ምንም ምክንያት የለም::

**2) ከዚህ በፊት ከወያኔ ጋር ከተደረጉ ድርድሮች ያገኘናቸው ተመክሮዎችና ከዚህ በመነሳት ወደፊት በሚደረጉ ምንም አይነት ድርድሮች እንዳይደገሙ ለመጠበቂያ የሚሆኑ ከአሁኑ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች**

ከማንኛውም ወገን ጋር የሚደረግ ድርድር የተደራዳሪዎቹ ምንነት፤ ውስጣዊ ባህርያቸውን፤ ከተለምዶ ተግባራቸው ያላቸውን ተአማኒነትና ወደዚህኛው ድርድር ያመጣቸውን ምክንያቶች በበቂ ከመገንዘብ ጋር ተያይዞ የሚታይ ጉዳይ ነው:: ቃሉን አክባሪና ተዓማኒ ከሆነ ሰው ጋር የሚደረግ ድርድርና ያለፈው ታሪኩ ታሪኩ ምንም አይነት የተዓማኒነት ባህርይ ከማያሳይ ቡድን ጋር የሚደረግ ድርድርም ሆነ ለድርድሩ የሚደረግ ዝግጅት ለየቅል ናቸው:: ይህ ማለት ግን ተዓማኒነት ካለው ኃይል ጋር ብቻ ነው ድርድር የሚካሄደው ማለት አይደለም:: በፍጹም ተዓማኒ ካልሆነ ኃይል ጋር የሚደረግ ማንኛውም ድርድር ግን ድርድሩ በእርግጥም ተግባራዊ ሊሆን ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ሊነጋ ሲል ይጨልማል

በመጽሀፍ ቅዱስ ታሪክ የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን ወይም በትንቢተ ሚልኪያስና በማቴዎስ ወንጌል መካከል ያሉት አራት መቶ አመታት "የዝምታ ግዜ" በመባል ይታወቃሉ። በእነዚህ አመታት የእስራኤል መንግስት በመጀመሪያ በፋርስ ከዚያም በሮማዉያን መንግስታት ቁጥጥር ስር የወደቀበትና እግዚአብሄርም በነቢያት በኩል መናገሩን ያቆመበት ግዜ ስለነበረ የእስራኤል ህዝብ አይኑ መልካም ነገር አይቶ ጆሮዉ መልካም ዜና ሰምቶ አያዉቅም ነበር። ይህ ደግሞ የሚገርም ነገር አይደለም። የሰዉ ልጅ ፈጣሪዉ ፊቱን ሲያዞርበትና አገሩ እሱ በማይፈልጋቸዉና ባልመረጣቸዉ ተባዮች ቁጥጥር ስር ስትወድቅ መልካም ነገር መስማት ቀርቶ ለአንድ ደቂቃም ቢሆን ሰለ መልካም ነገር ማሰብ አይችልም። የአገራችን የኢትዮጵያም ጉዳይ ከእስራኤል ህዝብ ጋር ተመሳሳይ ነዉ። በእርግጥ እግዚአብሄር ኢትዮጵያን መርጦ ለኢትዮጵያዉያን ብቻ የማይናገርበት ምንም ምክንያት የለም። ደግሞም ገየአገራችን ችግር ምንጩ ከላይ ከሰማይ ከእግዚአብሄር ሳይሆን እዚሁ ምድር ላይ ከእኛዉ ጋር የተያያዘ ነዉ። ነፃነት፤ ፍትህና ሰላም የናፈቀዉ የእስራኤል ህዝብ ከሜዶንና ከፋርስ ነገስታት ጭቆና ተላቅቆ እፎይ ብሎ ፈጣሪዉን ያመሰገነበት አፉ ሳይዘጋ ነዉ በሮማዉያን መገዛት የጀመረዉ። እኛ ኢትዮጵያዉያንም እንደዚሁ ነን። ከፊዉዳሉ ስርዐት ረመጥ ወጣን ብለን ስንዝናና ወታደራዊ አምባገነኖች በአቋራጭ መጥተዉ እንደ ሰነፍ ቆሎ 17 አመት አሹን። ወታደራዊዉን መንግሰት እየረገመ የመጣዉ የወያኔ አገዛዝ ደርግን ደምስሶ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ያሻረን መስሎን ነበር፤ ግን አገረሽብን እንጂ አላሻረንም።

ከየካቲት 1966 እስከ ዘንድሮ 2006 ዓም ድረስ ያለዉን የአርባ አመት ታሪካችንን በስዕላዊ መግለጫ መግለጽ ይቻላል፤ ወይም አርባ አመቱን በአንድ ቃል የጨለማ ዘመን ነዉ ብሎ መናገርም ይቻላል፤ አለዚያም በጽሁፍ ይገለጽ ከተባለም ዝርዝሩ እጅግ በጣም ብዙ ነዉና መጽሀፍ ሳይሆን መጻህፍት ሊያስፈልጉት ይችላሉ። ለሁሉም የታሪኩን ዝርዝር ለታሪክ ጸሀፊያን ትተን እነዚያን አርባ የጭንቀትና የመከራ አመታት በሁለት ግዙፍ ቃላት እንግለጽ ከተባለ እነዚያ ሁለት ቃላት "ደርግ" እና "ወያኔ" ናቸዉ። አዎ ደርግና ወያኔ አገራችን ኢትዮጵያን ላለፉት አርባ አመታት አንቀዉ ለያዟት ሽፋፋ የፖሊተካና የኤኮኖሚ ፖሊሲዎችና የእነዚህ ፖሊሲዎች ዉጤት ይዞት ለመጣዉ ብሄራዊ ዉድቀትና ዉርደት ግንባር ቀደም ተጠያቂዎች ናቸዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ አንዴ የጦርነት፤የድርቅና የስደት ታሪኩን ሌላ ግዜ ደግሞ ከሚረግጡት፤ከሚያስሩትና ከሚገድሉት ጨቋኝ ገዢዎቹ ጋር ያደረገዉን የመብት፤የነጻነትና የዲሞክራሲ ትግል ታሪክ እየዘከረ ዘመን መቁጠር ከጀመረ ብዙ አመታት ተቆጥረዋል። ይህ ስልጣኔን ከብዙ አገሮች በፊት የቀመሰዉና የክርስትናና የእስልምና ሐይማኖቶችን ከ1500 አመታት በላይ ጎን ለጎን ያስተናገደ ጨዋና አርቆ አሳቢ ህዝብ ለጨዋና ለአርቆ አሳቢ መሪዎች ባለመታደሉ "መልካም ነገር አሰማኝ" ብሎ ፈጣሪዉን ከመለመን ዉጭ መልካም ነገር ሰምቶ አያዉቅም። እኛ ኢትዮጵያዉያን ከቅኝ አገዛዝ ነፃ እንዲወጡ የታገልንላቸዉ የአፍሪካ አገሮች ጥለዉን ሲሄዱና ቆመን የጠበቅናቸዉ አገሮች የቆምንበት ቦታ ላይ ወደ ኋላ እያዩን ሲስቁብን፤ እኛ ለመልካም አስተዳደርና ለአስተዋይ መሪዎች ያልታደልነዉ ኢትዮጵያዉያን ግን ባለንበት መርገጥ ከጀመርን ሃምሳ አመት አለፈን። በደርግ ዘመንማ ባለንበት መርገጡ እራሱ ናፍቆን ጭራሽ ጉዟችን እንደ ግመል ሽንት ወደኋላ ሆኗል። ዛሬ ዕድሜያቸዉ ሃምሳና ከሃምሳ በታች የሆነ ኢትዮጵያዉያን መልካም ዜና ሳይሰሙ ከልጅነት ወደ ሽምግልና ሲሸጋገሩ በወያኔ ዘመን ተወልዶ ያደገዉ አንድ ትዉልድ ደግሞ ጭራሽ እዉነት የሚባል ነገር ሳይሰማ ሚስት አግብቶ ልጅ ወልዷል።

የስመ ጥሩዉን የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴና የ1966ቱን ከዳር እስከ ዳር ሁሉን ያቀፈ ህዝባዊ እንቅስቃሴ እንደ መሰላል ተጠቅሞ ለ17 አመታት እራሱን ያነገሰዉ ደርግ በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ በጥቁርነቱ ብቻዉን የሚጠቀስ ጨለማ ዘመን አስመዝግቦ አልፏል። "በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቤን አጣሁት" እንደሚባለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆቹ አፋፍመዉ እሱ ባነደደዉ የለዉጥ እሳት እሱ እራሱ እየተለበለበ 17 የቃጠሎ አመታት አሳልፏል። በእነዚህ አመታት የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆቹ ተገድለዉ ትኩስ አስከሬናቸዉ እንደ ግንቦት ልደታ ዶሮ በራፉ ላይ ተጥለዋል፤ የተገደሉ ልጆቹን ለመቅበር የጥይት ዋጋ ክፈል እየተባለ ተላግጦበታል። ነጋዴዉ ሸቀጥ ደብቀሃል ተብሎ የፍየል ወጠጤ ተዘፍኖበታል፤ገበሬዉ ከአማጽያን ጋር አብረሀል እየተባለ መንደሩ ተቃጥሏል፤ ወጣቱ አይኔ እያየ አልታረድም እያለ ተወልዶ ያደገባትን አገር እየተሰናበተ ወደ ጎረቤት አገሮች ተሰድዷል። ምሁሩ ጠመንጃ ተደግኖብኝ አልሰራም እያለ ወደ ምዕራባዉያን አገሮች ተሰድዶ እየተሰደደ ለባዕዳን የእዉቀት ምንጭ ሆኗል። በአጠቃላይ በ17ቱ የደርግ የጨለማ አመታት የኢትዮጵያ ህዝብ "አረ አይነጋም ወይ" እያለ አንገቱን አጎንብሶ የእንጉርጉሮ ኑሮ ኖሯል።

ወያኔ ትግራይን ከተቆጣጠረ በኋላ በጎንደር፤ በባህርዳርና በአምቦ በኩል እየመጣ ጥይት ሲያጮህ ለወትሮዉ ለጠላት ቀዳዳ የማይሰጠዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔን ዝም ብሎ ያሳለፈዉ አንድም ከደርግ የከፋ ምንም ነገር አይመጣም በሚል አለዚያም ወያኔ ሰራሹን ኢህአዴግ የኔም ልጆች አሉበት በሚል እምነት ነበር። ወያኔ ግን አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ ችኮላዉና ጥድፍያዉ ኢትዮጵያንና "ኢትዮጵያዊነትን" መግደል እንጂ የህዝብና የአገር አጀንዳ ጉዳዩም አልነበረም። ወያኔ ከጫካ ዉስጥ ጀምሮ ተዘጋጅቶ የመጣዉ ኢትዮጵያን፤ ህዝቧንና ታሪኳን ምን ያህል እንደሚጠላ ለማሳየት ነበርና ፀረ ህዝብነቱንና ዘረኛነቱን ለማወቅ የኢትዮጵያ ህዝብ መንፈቅ አልፈጀበትም።

ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት ወያኔ እነ እገሌን ገደለ፤ እነ እንቶኔን አሰረ፤ ድንበር ቆርሶ ለገረቤት አገር ሰጠ ወይም የአገራችንን ገበሬ አፈናቅሎ መሬቱን ለባዕዳን ሰጠ እያለን የወያኔን ወንጀሎች ብንዘረዝር ወይ ጊዜያችንን በከንቱ እናባክናልን አለዚያም የአድማጭን ጆሮ እናደነቁራለን እንጂ የወያኔ ወንጀል ተዘርዝሮ አያልቅም። ሆኖም ወያኔ ወንጀል ኢትዮጵያዉያንን በዓለም ዙሪያ ሁሉ ተከትሏቸዉ የሚሄድ ወንጀል ስለሆነ ይህንን ድንበር ዘለል ወንጀል በሚገባ መናገሩ ለህዝብ ማሳወቁ ጠቃሚ ነዉ ብለን እናምናለን። ወያኔ የኔ ነዉ ከሚለዉ ቡድን ዉጭ የሆነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሁለተኛ ዜጋ ነዉ፤ ግን ሁለተኛ ዜግነቱም የሚጸድቅለት ለወያኔ ግለሰቡ ለወያኔ የሚሰግድና የወያኔ ታማኝ አገልጋይ ከሆነ ብቻ ነዉ፤ ከዚህ በተጨማሪ ዜጎች ለፖለቲካና ለኤኮኖሚ መዋቅሮች የሚኖራቸዉ ቅርበት የገዢዉ ፓርቲ ደጋፊ ወይም ተቃዋሚ መሆናቸዉ እየተለየ ነዉ። ይህ ሁሉ የሚያሳየን አንድ ኢትዮጵያዊ "የወርቃማዉ ዘር" አባል ካልሆነ ለወያኔ ካልሰገደ ወይም የወያኔ ስርዐት ደጋፊ ካልሆነ በወያኔ ቤት አንደ ኢትዮጵያዊ አይቆጠርም፤ ለዚህ ነዉ ዛሬ ኢትዮጵያዉያን ዕድሜ፤ፆታ፤ሀይማኖትና የትምህርት ደረጃ ሳይለያቸዉ ሁሉም ኢትዮጵያን ለቅቀዉ ለመዉጣት የህይወት መስዋዕትነት የሚከፍሉት።

ከወያኔ የዘረኝነት ፖሊሲ ለመገላገልና ኢትዮጵያ ዉስጥ ስራ እየሰሩ መኖር ባለመቻላቸዉ ወደ ተለያዩ የአረብ አገሮች የሚሰደዱት ወገኖቻችን የሚደርስበቸዉን ግፍና መከራ በተደጋጋሚ ሰምተናል። ከሰሞኑ ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ ኢትዮጵያዉያን እየደረሰባቸዉ ያለዉ ግፍ፤ መከራና ዉረደት ግን በአይነቱም በስፋቱና በክፋቱ እስከ ዛሬ ድረስ ካየናቸዉ ችግሮቻችን ሁሉ የተለየ ነዉ። ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያዉያንን የኔ ዜጎች ናቸዉ ብሎ የሚያስብላቸዉና የሚከራከርላቸዉ መንግስት እንደሌለ በዉል የሚያዉቁት ሳዑዲዎች ወገኖቻችንን ከሰብዓዊነት ዉጭ በሆነ መንገድ ደብድበዋል፤ አስረዋል፤ ገድለዋል። ይህ ላለፉት አራት ሳምንታት የዓለምን ህዝብ ሁሉ ያናገረና ያሰቆጣ ድርጊት በወገኖቻችን ላይ ሲፈጸም የልተቆጣ፤ ያልተናገረና ሆዱ ያልባባ ቢኖር ወያኔ ብቻ ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ያለፉትን ሃምሳ አመታት ያሳለፈዉ ከገዢ መደቦች ጋር እየታገለ ነዉ። በዚህ የትግል ሂደት ዉስጥ ሁለት መንግስታትን አስወግዶ ዛሬ ከሦስተኛዉ ጋር እየተናነቀ ይገኛል። ዛሬ ወያኔን በተለያየ መልኩ አምርረዉ የሚታገሉ ኃይሎች በህይወታቸዉ ቆርጠዉ ትግል ዉስጥ የገቡት በ1966 እና በ1983 ዓም የኢትዮጵያ ህዝብ ህዝብ ትግል ከገጠመዉ ሁለት ታሪካዊ መሰናክሎች ትምህርት ቀስመዉ ይመስለናል። እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ወያኔን የመሰለ አገርና ህዝብ ያዋረደ ዘረኛ ድርጅት ተሸክሞ ይህንን ሁሉ አመት መዝለቁ በራሱ ትልቅ ጥፋት ነዉና እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊም ከዚህ ጥፋት ተማሪ ይመስለናል። ወያኔ በገጠመዉ ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃዉሞና ከዉስጡ በተነሳ ቅራኔ ተወጥሮ ለመዉደቅ እየተንገዳገደ ነዉ። ሆኖም ወያኔ ተንገዳገደ ማለት በራሱ ወድቆ ይሰበራል ማለት አይደለም። ስለዚህ መልካም ዜና የናፈቀን፤ ፍትህ፤ ዲሞክራሲና እኩልነት የናፈቀን ዜጎች አንድ የምንሆንበትና በተባበረ ክንድ በመንገዳገድ ላይ የሚገኘዉን ወያኔን ገፍተን የምንጥልበት ግዜ አሁን ነዉ።

ወያኔ በእኛና በነጻነታችን፤ በእኛና በዲሞክራሲ መካከል የገነባዉ የብረት ግድግዳ ወደ ግባችን ከመድረስ በፍጹም ሊያግደን አይገባም። ይልቁንም የዚህ ግድግዳ መኖር የእልህችን ማሳያ፤ የጽናታችን ምንጭና የቁርጠኝነታችን ምልክት ሊሆን ይገባል። እንዲህ አይነት ህዝባዊ የትግል ፍላጎትና ቁርጠኝነት ካለን የዝምታ፤ የስደት፤ የእስር፤ የግርፋትና የግዲያ አመታቶቻችን ያበቃሉ። ያለቀስነዉ ለቅሶ፤ ያነባነዉ እምባና የታገልነዉ ትግል የአርባ አመት የጨለማ ዘመናችንን በብርሃን ይለዉጠዋል፡፤ መልካም ነገር መስማት የተሳነዉ ጆሯችን መልካም ነገር ይሰማል፤ የራሱን ራዕይ እንዳያይ በገዢዎቻችን መጋረጃ የተሸፈነዉ አይናችን መጋረጃዉን በጣጥሶ አዲስ ራዕይ ያያል። እኛም በገዢዎቻችን ግልምጫ ሳይሆን በራሳችን ራዕይ የምንመራ ነጻ ህዝብ እንሆናለን። አዎ ነጻ ህዝብ! እራሱን በእራሱ የሚመራ ነጻ ህዝብ፤ በኋላ ቀርነቱ ተቆጭቶ ለስልጣኔ የሚሮጥ ነጻ ህዝብ፤ ተከባብሮ በእኩልነት የሚኖር ነጻ ህዝብ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ አንዴ ነጻነቱ እጁ ከገባ በኋላ ነፃነቱን የማያስጠብቅ ነፃ ህዝብ እንሆናለን። የራሱን የማይሰጥ የሌሎችን የማይነካ ነፃ ህዝብ፤ የራሱንና የጎረቤቶቹን ሰላም የሚያረጋግጥ ነፃ ህዝብ፤ ሰብዓዊ መብቶችና ፍትህ ሲረገጡ ቁጭ ብሎ የማያይ ነጻ ህዝብ እንሆናለን። አርባ አመት ሙሉ ያስተኛን ረጂም ሌሊት ይነጋል። አረ አይነጋም ወይ፤ አይነጋም ወይ . . . አይነጋም ወይ ሌቱ ኢትዮጵያዬ . . ማማዬ። ቴዲ አይዞህ ላንተም፤ ለእነሱም ፤ ለእኛም ለሁላችንም ይነጋል።

## የወያኔ አገዛዝ ከአለማችን ሙሰኛ አገሮች ግንባር ቀደሙ መሆኑ ይፋ ሆነ

ህዳር 24 ቀን 2006 ዓ.ም. በመላው ዓለም ይፋ የሆነው የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ተቋም የሙስና አመላካች ሪፖርት፣ ወያኔ የሚገዛት ኢትዮጵያ ከሙስና ጽዱነት ተርታ ውጭ ከሆኑና በሙስና ተግባር በከፍተኛ ደረጃ ከሚፈረጁ አገሮች አንዷ መሆኗን ይፋ አድርጓል።

ሪፖርቱ በሚከተለው የሙስና መለኪያ ሚዛን መሠረት፣ ከሙስና ጽዱ የሚባሉ አገሮች ከዘጠና እስከ መቶ ነጠብ የሚያገኙት ሲሆኑ በተቃራኒው ከፍተኛ ሙስና ተንሰራፍቶባቸዋል፣ ተብለው የሚታሰቡ አገሮች ደግሞ ከመለኪያው ከ50 በመቶ በታች የሚያስመዘግቡት እንደሆኑ ገልጾ፡ በመንግሥት ተቋሞች ውስጥ ከፍተኛ ሙስና ተንሰራፍቶባቸዋል ተብለው ከተለዩት ውስጥ ኢትዮጵያ 33 ከመቶ የመለኪያውን ነጥብ በማስመዝገብ ከከፍተኛ ሙሰኞች ተርታ እንደምትሰለፍ የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ሪፖርት ይፋ አድርጓል፡፡ ከ177 አገሮች ውስጥ 111ኛውን ደረጃ መያዟም በሪፖርቱ ይፋ ሆኗል፡፡

ኢትዮጵያን ጨምሮ መላው አገሮች ለሙስና ተጋላጭነት ከሚለኩባቸው መመዘኛዎች መካከል፣ የፕሬስ ነፃነት፣ የተጠያቂነትና የሰዎች የመደመጥ መብት፣ የፍትሕ አካላት ከተፅዕኖ ነፃ መሆን፣ የሕግ የበላይነት፣ የሰብዓዊ ልማት መለኪያና ሌሎችም ጠቋሚዎች እንደሚካተቱ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል በድረ ገጹ ይፋ አመላክቷል፡፡

ይህው ጥናቱን ያዘጋጀው ተቋም ኢትዮጵያ በፕሬስ ነፃነት ከመጨረሻዎቹ የፕሬስ ነፃነት ከሌሉባቸው አገሮች ተርታ መሆኗን እና የፍትህ አካላቱም ነጻ ያልሆነና በመንግስት ተጽእኖ ስር መሆኑን ጨምሮ ገልጿል፡፡ ከዚህ በፊት ከ1997 ምርጫ በኋላ ታዋቂና ባለሌላ ማዕረግ አማራ ጄኔራሎችንና የጦር አዛዦችን ጨምሮ ብዙ የጦሩ አባላትን ከቅንጅት ጋር በተያያዘ ከሶ ዘብጥያ በማውረድ የሞት፣ የእድሜ ልክና ከፍተተኛ ዘመን እስራት ማስፈረዱ የሚታወስ ሲሆን ይህ የፋሽስት ወያኔ ርምጃ ግን ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል እንዳላቆመውና እስካሁንም የቀጠለ መሆኑ ተያይዞ ተጠቅሷል።

## ኢትዮጵያዉያንን ቀጥረዉ የሚያሰሩ የሳዑዲ ዜጎች ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸዉ

ፋሽስት ወያኔና ቴዎድሮስ አድሃኖም ይህን ያህል ሽ መለስን ያን ያህል ደግሞ ዛሬና ነገ ይገባል እያሉ ከቁጥር ጋር በመጫወት ለራሳቸው የፖለቲካ ስእልና ለቀጣይ ሀገራዊ ምርጫ ራሳቸውን እያዘጋጁ ባሉበት ባሁኑ ሰአት ወገኖቻችን ግን እውነተኛ የሞት አደጋ አንዣበባቸው ይገኛል። በሌላ በኩል ከሳውዲ አረቢያ በተገኘ ገንዘብ ሃላፊነቱን ወስዶ ተጎጂዎችን በማመላለስ ላይ ያለው አይ.ኦ.ኤም. መልሻለሁ የሚለውና ፋሽስት ወያኔና ቀጣይ ጠቅላይ እሆናለሁ ብሎ ላይታች የሚለው ቴዎደሮስ መልሰናል የሚሉት የሰማይና የመሬት ያህል የተራራቀ መሆኑ ብኑዎቹን አስደምሟል። ፋሽስት ወያኔ በእንዲህ ያለ ፈታኝ ወቅት እንኳ ሳይቀር የበለጠ የሚያሳስበው ስልጣኑና የራሱ ፖለቲካ እንጅ ሕዝባችን እንዳልሆነ አስመስክሯል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ ወር ባስቆጠረዉ የሳውዲ ጥቃት እስካሁን በርካታ ኢትዮጵያዊያን የተገደሉ ሲሆን፣ በፖሊሶች እና በሃገሪቱ ዜጎችም በኢትዮጵያውያን ሴቶች ላይ ጾታዊ ጥቃት በከፍተኛ ደረጃ እየተፈጸመ እንደሆነ የተለያዩ መገናኛ ብዙሀንና ድህረገጾች መዘገባቸው ይታወቃል።በዚህም ምክንያት ከአካል ጉዳት በተጨማሪ ከፍተኛ የስነልቦና ችግር እና የአእምሮ መቃውስ የደረሳባቸው ኢትዮጵያዊያን ቁጥር እጅግ ማሻቀቡ ታውቋል። አብዛኞቹ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ በየእለቱ ዘግናኝ ድብደባ እየተፈጸመባቸው እንዲሁም በርሃብ እና ውሃ ጥም እየተቀጡ ምድረ በዳ በሆነ በርሃ ማጎሪያ ጣቢያ እንዲቀመጡ እንደተደረጉ ከስፍራው የሚወጡ መረጃዎች ይፋ አድርገዋል።ይህ በንዲህ እንዳለ በሰሜን አሜሪካ፣ አውሮፓ እና በሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ጥቃቱ መፈጸም ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ታላቅ ተቃውሞና ቁጣቸውን በወያኔው ኤምባሲና በሳውዲ አረብያ መንግስት ላይ እያሰሙ ይገኛሉ፡፡ ይህ የኢትጵያዊያን ተቃውሞ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ጠንካራ የአንድነት ስሜት የተንጸባረቀበት ሲሆን የወያኔ አገዛዝ የወሰደውን ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ህዝብ አቋም በእጅጉ የተቸ እና የሳውዲ አረብያ መንግስት እየወሰደ ያለውን እርምጃ ለመላው የአለም አቀፍ ማህበረሰብ ያጋለጠ ነው፡፡ የወያኔ አገዛዝ በዜጎቹ ላይ እየተፈጸመ የሚገኘውን ይህንን ዘግናኝ ድርጊት ለመከላከል ፈጣን እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ በሁኔታው ተራ የፖለቲካ ፕሮፖጋንዳ ትርፍ ለማግኘት ላይ ታች ማለቱን ተያይዞታል፡፡ የወያኔ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተብዬ ቴዎድርስ አድሃኖም በየእለቱ የሚሰጠው መግለጫ እርስ በእርሱ የሚጋጭ እና ተዓማኒነት የጎደለው ስለመሆኑ በርካቶች በተለያዩ ድረገጾቻቸው እየገለጹ ሲሆን የወያኔው አገዛዝም አጋጣሚውን በመጠቀም ቴዎድሮስ አድሃኖምን ለወገን ተቆርቋሪና አሳቢ በማስመሰል ለሚቀጥለው የጠቅላይ ሚኒስቴርነት ቦታ እያመቻቸው እንደሆነ በሰፊው ይነገራል።

## የወያኔ አገዛዝ በመልዕክተኞቹ በኩል ላቀረበው የ"እንደራደር" ጥያቄ ከግንቦት 7 . . . ( ከገጽ 2 የዞረ )

የሚችል መሆኑን የሚያሳዩ ጠንካራ መጠበቂያዎች (System of Verification) እንዲሁም ግልጽ የመተግበሪያ ሥርዓቶች (Implementation Mechanism) ሲደረጉለት ብቻ ነው ከምር ሊወሰድ የሚችለው:: ከዚህም ባሻገር ግን መጀመሪያውኑ ወደ ድርድር የሚመጣው ለጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ሳይሆን በእዉነተኛ መንፈስ ከድርድር የሚመጣውን ውጤት በመፈለግ መሆኑን የሚያሳዩ "የመተማመኛ" ምልክቶች ሲያሳይ ነው በእርግጥም ወደ ድርድር የመጣው ከልቡ ድርድሩንና ከድርድሩ የሚመጣዉን ዉጤት ፈልጎ መሆኑን ለማመን የሚያስችለው::

ወያኔ ከተቀናቃኝ ወገኖች ጋር "ድርድር" ሲያደርግ የመጀመሪያ ጊዜዉ አይደለም:: እኛ እስከምናውቀው ድረስ ምናልባት በኃይል ይበልጡኛል ብሎ ከሚያምናቸው ወገኖች ጋር ካልሆነ በስተቀር፣ በረሃ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በማንኛውም ጊዜ ለቃሉ ታማኝ፤ ለመርሁ እውነተኛ፤ ለደረሰበት ስምምነት ተገዢ ሆኖ አያውቅም:: ይልቁንም ሶስተኛ አደራዳሪ ወገኖችን በሚያሸማቅቅና በሚያሳፍር መልኩ ውሸትን እንደ አዋቂነት፤ ማጭበርበርን እንደ ብልጠት፤ የተስማማበትን በገሀድ ማፍረስን እንደ የአመራር ብልሀት አድርጎ የሚያይ፤ ምንም እፍረትና ጨዋነት የሚባል ነገር ያልፈጠረበት እኩይ ኃይል ነው:: ከራሱ የድርጅት ጥቅምና በስልጣን ከሚገኝ የዝርፊያ ሀብት ማካበት ባሻገር፤ ለአገር ዘላቂ ጥቅም ብሎ የራሱን ጥቅም አሳልፎ የሚወስደው ምንም እርምጃ እንደሌለ በተግባር በተደጋጋሚ ያረጋገጠልን ኃይል ነው:: በግንቦት 7 ውስጥ ያለን ወገኖች ይህንን የወያኔ ባህርይ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ሌሎች ጽፈውት ያነበብነው ሳይሆን፣ እራሳችን በተግባር በተሳትፈንበት ሂደት ያገኘነው ጥልቅ ግንዛቤ ነው:: ይህንን ደግሞ በአንድ አጋጣሚ ብቻ ሳይሆን ከድርጅቱ ታሪክ ጋር የተጣበቀ፤ በአመራር አባላቱ ላይ እንደ ግል ባህርይ የሰረጸ መሆኑን እስከንገነዘብ ድረስ በተደጋጋሚ የተመለከትነው ነው:: ስለዚህም ከዚህ ኃይል በኩል የሚመጣን የ "እንደራደር" ጥያቄ ከዚህ በፊት እንዳደረገው ለገባበት የፖለቲካ ውጥረት ማስተንፈሻ፣ ለውሸት ፕሮፓጋንዳው መጠቀሚያ፤ ለጊዜያዊ የፖለቲካ ትርፍ መሰብሰቢያ፤ የዴሞክራሲ ታጋዮችን ትጥቅ ማስፈቺያና ወኔ መስለቢያ አድርጎ እንዲጠቀምበት በፍጹም አንፈቅድለትም:: ስለዚህም ከላይ በመርህ ደረጃ ከጠቀስናቸው ሶስት ጉዳዮች በተጨማሪ ምንም ዓይነት ድርድር ከመደረጉ በፊት ወያኔ ጉዳዩን ከምር የወሰደው መሆኑን የሚያሳዩ "የመተማመኛ" እርምጃዎች መውሰድ አለበት ብለን እናምናለን:: እነኝህም፣

ሀ) ሁሉንም የፖለቲካ እስረኞች፤ ጋዜጠኞች፤ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፍታት:: ይህ ደግሞ በግልጽ የሚታወቁ እስረኞችን ብቻ ሳይሆን በድብቅ የተቋቋሙ ማጎሪያና ማሰቃያ ቤቶች ያሉትን ሁሉ ማጠቃለል አለበት።

ለ) በሕዝብ በተለይ በተቃዎሚ ኃይሎች ላይ ወያኔ በየቀኑ እያካሄደ ያለውን ወከባና እንግልት ባስቸኳይ ማቆም፣ ሰብዓዊና የዜግነት መብታቸውን ማክበር አለበት።

ሐ) በፖለቲካ ምክንያት ከዚህ በፊት የተወሰዱ ሁሉም ዓይነት ፍርድ ተብዮ ውሳኔዎች እንዲሻሩ ማድረግ፤ በሂደት ላይ ያሉ ከፖለቲካ ጋር የተያያዙ ምንም አይነት ክሶችን ማቋረጥ አለበት።

መ) ሕዝብን በፍርሃትና በስጋት ለማቆየት ሆነ ተብለው የወጡ አፋኝ ህጎችን በአስቸኳይ ማንሳት አለበት።

ሠ) ማንኛውም ድርድር ገለልተኛ የሆኑ ሶስተኛ ወገኖች ባሉበት፤ የድርድሩ ሂደት በምስልና በድምጽ ተቀርጾ በገለልተኛ ወገኖች እጅ ብቻ የሚቀመጥ፣ የድርድሩ ቦታም የተደራዳሪ ወገኖች በጋራ በሚስማሙበት ቦታ መሆኑን መቀበልና ይህንንም በግልጽ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማሳወቅ አለበት።

እነኝህ ከላይ ያስቀመጥናቸው በወያኔ በኩል የሚወሰዱ "የመተማመኛ" እርምጃዎች ለተቃዋሚዎች ተብሎ የሚወሰዱ እርምጃዎች አይደሉም:: ወያኔ እነዚህን እርምጃዎች ለመውሰድ ቁርጠኝነት ሳይኖረው ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመስረት የሚደረግ ድርድር ላይ ከምር ይሳተፋል ብለን ማመን በፍጹም ስለማንችል ነው::

እስከዚያው ድረስ ግን ግንቦት 7ም ሆነ ሌሎች ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመስረት በቁርጠኝነት የምንታገል ኃይሎች፣ ወያኔ እነኝህን የመተማመኛ እርምጃዎች እስኪወስድና ቀደም ብለው በተቀመጡት መርሆች መሠረት በሚደረግ ድርድር በተግባር ሊመነዘር የሚችል ስምምነት፣ አልፎም ለምንም አይነት ማጭበርበርና መንሸራተት እድል የማይሰጥ ጠንካራ መጠበቂያዎች መኖራቸው እስኪረጋገጥ ድረስ፣ የጀመርነውን ትግል ይበልጥ አጠናክረን የምንገፋበት እንጂ በምንም አይነት ለአንድ አፍታም ቢሆን በድርድር ስም የማንዘናጋ መሆኑን አበክረን እናስታውቃለን::

የግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣

ኅዳር 25፣ 2006 ዓ:ም


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቂያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ማን ነው የተዋረደው?

ይሄይስ አእምሮ ( ክፍል 2 )

ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ እየደረሰ ያለው መከራና ውርደት ወቅቱን ጠብቆ ነገ በሌላ ሕዝብና መንግሥት ላይ ይደርሳል - እንደእስካሁኑ ሁሉ። ይህ አነጋገር የትንቢት ጉዳይ ሣይሆን ማንም አእምሮ አለኝ የሚል የዓለም ዜጋ ሁሉ ሊረዳው የሚችል ነባራዊ እውነታና የማይሸሹት ወረፋ ነው - ወረፋ እስኪደርስ ያለው የጊዜ እርዝማኔ እያነሆለላቸው ብዙዎች ይሞኛሉ። ያዋጣ የነበረው አካሄድ ግን በምንም ዓይነት የልዩነት አጥር ራስን ሳያካልሉ በሰው ልጅነት ብቻ አንዱ የአንዱን ችግር ለማስወገድ መጣር ነበር። በሆነ አጋጣሚ አንድኞችን ከሌላኞችን በተለዬ ሁኔታ ወደአውሬነት በምንለወጥበትና እንደሳዑዲዎች አንድ ምሥኪን ወገን ላይ ቀን የሰጠንን ኃይልና ጉልበት በምናሳይበት ጊዜ በዝምታና በአግራሞት ማለፍ ሣይሆን ሃይ ብንልና ብናስቆም ተጠቃሚዎቹ ሁላችንም የሰው ዘሮች በሆንን ነበር። ሰዎች ግን ለዚያ አልታደልንምና የዘራነውን እንዳጨድን ዝንታለማችንን በየተራ ስናለቅስ እንኖራለን። ወደኋላው ላይና ቋቱ ሲሞላ ግን ሁላችንም በኅብረት የምናለቅስበት ዘመን መምጣቱ አይቀርም - ያኔ ታዲያ አልቃሽም አስለቃሽም፣ ፊሽካ ነፊም አስተኳሽም … ሁሉም ተያይዞ የደም ዕንባ እንደጎርፍ ያወርዳል። የምናስቀምጠው ነገር ሁሉ የኛው ነው - ማንም አይወስድብንም። በባንክ የምናኖረውን ገንዘብ ሲያስፈልገን አውጥተን እንደምንጠቀምበት ሁሉ በሰዎች ላይ የምንሠራውን የግፍ መዝገብም ሁሉ የምናወራርድበት ጊዜ ሲመጣ በእጃችን የገቡ ሌሎች ምሥኪኖችን ባስለቀስነው መጠንና ከዚያም በላይ እኛም እናለቅሳለን። አሁን ግን በብረት አጥር ውስጥ የምንኖርና መቼም ቢሆን ምንም ችግር እንደማይደርስብን የምንቆጥር ወገኖች አንዳችን በአንዳችን ችግር እየተዝናናን መኖርን መርጠናል። የምንመርጠው መንገድ ሁሉ ግን አዋጭ ሊሆን እንደማይችል ከታላቁ መምህር ከታሪክ መማር በተገባን ነበር። ያለቀሱ ይደሰታሉ፤ ያስለቀሱም ያለቅሳሉ።

ዐረቦች በእኔ ዕድሜ ኢትዮጵያ ውስጥ በርሜል ገፊ ነበሩ። የሚገፉት በርሜልም የነዳጅ ሣይሆን የውሃ ነው። ከአምስትና ከአሥር ኪሎ ሜትሮች ከሚገኙ የወንዝና የጉድጓድ ውሃዎች በሸክናና በቅል እየቀዱ ሃዲድ በተገጠመላቸው በርሜሎች በመግፋት ለሀብታም ኢትዮጵያውያን እየሸጡ በሚያገኙት የላብ ፍሬ ይተዳደሩ ነበር - የዛሬውን አያድርገውና። ዛሬና አሁን ግን ያን መገፋታቸውን ፈጣሪ ተመልክቶ ይሄውና በየሥፍራው እንደምንጭ እየቆፈሩ በሚያወጡት ነዳጅ ጠግበው ይሠሩትን አጥተዋል። ለዚህም ያበቃቻቸው ባለብዙ ካርድ ሀገር የሆነችው አሜሪካ ናት። ገንዘብ በፍጥነት የሚገባለት ጭንቅላት ውስጥ ደግሞ የሚያስብ አንጎል አይኖርም፤ ገንዘቡ ወደ ኪስ ሲንዶለዶል አንጎል ከጭንቅላት እየወጣ ወደከርስ ወርዶ ይደበቃል። ዐረብ ደግሞ ስናየው አብዛኛው ሃይማኖት የለሽ ጥጋበኛ ነው። እንደዐረብ አስመሳይና መረን የለም። ዕውቀቱ ሣይኖር ፔትሮዶላሩ ተትረፈረፈላቸውና የሚሆኑትን አጡ። ዕድሜ ለአሜሪካ ሥልጣኔን በገንዘባቸው ከአሜሪካና አውሮፓ አመጡላቸው - ዐረቦች የዛሬ ስንት ዓመት ከተማቸውን በፍየልና በዓሣሞች ያስጸዱ እንዳልነበር ዛሬ የሀበሻ ጉልበትና የአሜሪካን ቴክኖሎጂ አጠገባቸው። እነዚህ ለይስሙላ “አላሁአክበር” እያሉ ሃይማኖት ያላቸው የሚመስሉ ስድ ሰዎች በተለይ ሀብታሞቹና የቤተ መንግሥት ልዑላኑ የሚሠሩትንና በኪታቦቻቸው የሠፈሩትን ቀኖና ሃይማኖት ብናስተያይ ከሞላ ጎደል ሁላቸውም የሰይጣን አምላኪዎች መሆናቸውን መረዳት አይከብደንም። እነዚህ የለዬለትን ጥቁር ሰይጣን አምላኪ ዐረቦች በግልጽ ባይሆንም ብዙዎቹ በኅቡዕ ሉሲፈርን ከሚያመልኩ የሩቅ አጋሮቻቸውና የሀብት ተጋሪዎቻቸው ነጫጭባዎች ጋር እየተመሣጠሩ ዓለምን ከሃይማኖት፣ ከሞራልና ከባህላዊ ትውፊቶች አንጻር እያላሸቋት ይገኛሉ። የሁለቱም እምነት አንድ ነው፤ በገራምነት ሉሲፈር የተሻለ ቢሆንም ሲመጣበት ከሰይጣን ባልተናነሰ ቁጡ ነው፤ ለአንድ ክፋት ተመጣጣኝ ደግነት እንዳለው የሚያምኑት ሉሲፈራውያን ለጥቅማቸው ሲሉ ከሰይጣናውን በማይተናነስ ሁኔታ ዓለምን እስከመሸጥና መለወጥ ይደርሳሉ። የሁለቱም የእምነት መሠረት ገንዘብ ነው። ገንዘብ ሁሉን ያደርጋልና ሥልጣንንና ገንዘብን የተቆጣጠረ ወገን ሁሉ ያሻውን መሆንና ማድረግም ይችላል። ዴሞክራሲ፣ ፍትህና ነጻነት ጭምብሎች ናቸው - ለሁሉም እኩል የማይሠሩ የሚጠሉትን የማንበርከኪያ ካርዶችም ጭምር። ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ የተባለው ለጊዜውና በአሁኑ የዓለማችን ቅርጽ እውነት ነው።

ገንዘብ ካለህ ዴሞክራሲን ከአሜሪካም ሆነ ከእንግሊዝ ትገዛለህ፤ ገዝተህም ለሕዝብህ ታድላለህ፤ አድለህም “ዴሞክራሲን ለሕዝቤ አደልኩ!” ብለህ ብትናገር ትታመናለህ። ባትታመንም በዴሞክራሲያዊነትህ ተቀባይነትን አታጣም። ዕድሜ ለገንዘብህ። ድሃ ከሆንክ ግን በኢዴሞክራሲያዊነት፣ በአሸባሪነት፣ በሰብኣዊ መብት ጣሽነት፣ በምርጫ አጭበርባሪነት፣ … ትወቀሳለህ፤ ወደ ጓንታናሞ ልትላክና ልትበሰብስ ዕድል ከቀናህም ወደዘሄግ የነሱው መሣሪያ ልትቀርብ ትችላለህ። በአይኤም ኤፍና በዓለም ባንክ ልምጮችም ልትሸነቆጥ ትችላለህ፤ በልዩ ልዩ ማዕቀቦችና ጠና ሲልም በኔቶ ጦርና በተናጠል የኃያላን ብትርም ልትኮረኮም ትችላለህ። ዓለማችን እንዲህ ዐይናቸውን በጨው ባጠቡና ባፈጠጡ መድሎዎች የተሞላች ናት። አንበሣ ምን ይበላል ተበድሮ ምን ይከፍላል ማን ጠይቆ ነው ነገሩ - ግን አይምሰልህ - የቀንም ቀን አለው፤ የጀግናም ጀግና አለው፤ ፍርድ ቢዘገይ አይቀርም። እናም ወዮ እንላለን - ወዮ ለቀኑ። ከሳዑዲና ከመሰል ጭራቅና ሰይጣን መንግሥታት አንሶላ ለምትጋፈፈዋ የሉሲፈር ሀገር ወዮላት! የ”ወዮላት!” መንስኤውም ፍርደ ገምድልነቷና ያንን ተከትሎ ቢሊዮኖች መከራና ስቃይ ውስጥ መግባታቸው ነው - ሚዛናዊ ፍርድን የማያውቅ እንዲያውቅ የሚገደድበት አጋጣሚ ይመጣለታል - ወደደም ጠላም። ይህች ሀገር የምትለውንና የምትሠራውን አጥኑ። ያለባትንም ወዮታ ልብ በሉ። የአሁኑንም ብቻ አትመልከቱ። ለዚህ ለዚህማ ኢትዮጵያም በዓለም ከነበሩ አራት ኃያላን መንግሥታት አንዷና እስከየመንና ከዚያም ባለፈ የምታስገብር ታላቅ ሀገር ነበረች። ብዙ የአሁን ነገሮች ታሪክ የሚሆኑበት፣ ብዙ የወደፊት ነገሮችም የአሁን የሚሆኑበት ዕፁብ ድንቅ ሁኔታዎች ይከሰታሉና እንዳለ የሚቀር፣ እንደቀረም የሚኖር ነገር አለመኖሩን ማስታወስ ይገባል። ይህች ቀን በቅርብ ታልፋለች።…

በልጅነቴ ቤተሰብ ወደሱቅ ሄጄ ዕቃ እንደገዛ ይልኩኝ የነበረው “ዐረብ ቤት ሄደህ ይህን ዕቃ ገዝተህ ና!” እንጂ ወደሱቅ ሂደህ ይህን ወይ ያን ግዛ አይሉኝም ነበር። በ”ሰይቼንቶ ሄድኩ” ይባል የነበረውና አሁንም ድረስ በአንጋፋ ዜጎች የሚባለው የመጀመሪያዋን የጣሊያን ታክሲ መኪና እንደሚያስታውሰን ሁሉ ዐረብ ቤትም የሚያስታውሰን የሱቅ ሸቀጦች ይበልጡን በዐረቦች መጀመራቸውን ወይም በነሱ ይካሄዱ የነበረ መሆኑን ነው። ኢትዮጵያ ከእኛም በላይ የነሱ ቤት ነበረች። “ፈረስት ሂጅራ”ን ትተነው ትናንትናና ከትናንት ወዲያ በነገሥታቱ ዘመን የአሁኗ ኢትዮጵያ በልጽገውና ከብረው ከእኛው ባልተናነሰ እንዲያውም በበለጠ እየተዘባነኑ የሚኖሩባት የእኩል ሀገር ነበረች - ለነገሩ ኢትዮጵያ ለውጪዎች እንጂ ለራሷ ልጆች ሆና አታውቅም - ሀገራችን ብዙውን ጊዜ የሚጠቅማትን ከማይጠቅማት ያለመለየት ችግር አለባት። ዛሬ ወያኔ የሚባል ሀገር አጥፊ አንበጣና ተምች መላዋ ሀገራችንን ቀስፎ ስለያዛት የተለዬ ውርደት ገጠመንና ለዚህ ውርደት ተዳረግን እንጂ ዐረቦች ልብ ኖሯቸው እንዲህ ሊጫወቱብን የሚቃጡ አልነበሩም። ጊዜ ነው። ጊዜ ሁሉም ነገር ነው። ‹ጊዜ ባለውሉ› ሁሉንም ያሳያል። … ዕድሜ ከሰጠን ደግሞ ወደፊት ይህን ሂሳባቸውን ሲያወራርዱ እናይ ይሆናል። አንድዬን ለበቀልና ለአጸፋዊ ምላሽ ማን ብሎት? አሁን አሁንስ ፈጣሪ ለዚህ ተግባር ብቻ ያለ ይመስለኛል - ለቅጣትና የኃጢኣት ዋጋን ለመስጠት።

የሆኖ ሆኖ ግን ኢትዮጵያዊ መንግሥት ስለሌለን እየደረሰብን ያለው ይህ ግፍና ቅጣት በኛ ላይ ብቻ የወረድ የውርደትና ቅሌት መዓት ሣይሆን በሰው ልጆች ላይ እየደረሰ ያለ መቅሰፍት መሆኑን ልብ ማለት ይገባል። በሳዑዲ አንድ ዜጋ አለኃጢኣትና አለወንጀል ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ብቻ በጠራራ ፀሐይ ታረደ ማለት የታረደው ሰው በሃይማኖትና በፆታ ወይም በመልክዓ ምድር ሳይወሰን ነጭም ነው፤ ጥቁርም ነው፤ ቢጫም ነው። አለፍርድና አለአበሳው የታረደው ሰው ሁሉንም የሰው ዘር የሚወክል እንጂ አንድን ሀገር ብቻ ለይቶ፣ የአንዲትን ሀር ዜጎች ብቻ አጣቅሶ በውርደት የሚያስጠራ ክልላዊ ወይም ብሔራዊ ጉዳይ ብቻ አይደለም። ይህን ማድረግ ድፍረት እንጂ ሌላ ባለማስፈለጉ በማንም ላይ እንዲህ ማድረግ ቀላል ነው። በአሳቻ ቦታ አንድን ነጭ አሜሪካዊ ማረድ ወይም ጠቃሚ የሰውነት ብልቶቹን እያወጡ ለሀብታም መሸጥ ቀላል ነው። በአሳቻ ቦታ አንድን ነጭ እንግሊዛዊ ወይ ሞስኮባዊ ማረድ ቀላል ነው። በተመቸ ሥፍራ አንድን ነጭ እስራኤላዊ አንቆ በከንቱዎች ዘንድ መዘባበቻ ማድረግ ቀላል ነው - በአልቃኢዳዎች ሲደረግ የነበረም ነው። አደጉ ከተባሉ ሀገራት የተመለመሉና አንቱ በተባለ ዘመናዊ የጦር ሥልት ሠልጥነው ለግዳጅ የተሠማሩ “የሰለጠነው ሀገር” ወታደሮች ኢራቅ ውስጥ ሬሣ ላይ ሲሸኑ አይተናል፤ ያኔም በዓለም የሥልጣኔ ደረጃ “ምጥቀት” ተደንቀናል - ከዚህች ሰዎች ሰዎችን ከምድረ ገጽ ሊያጠፉ አሰፍስፈው ከሚታዩባት፣ የሞተ ሰውን ሳይቀር በ”ማሰቃየት” ሰይጣናዊ እርካታ ለማግኘት ከሚማስኑባት ከዚህች ድውይ ዓለም፣ ሳዑዲዎች እየፈጸሙት ከሚገኘውና ከመሳሰለው አረመኔነት ሌላ ምን ይጠበቃል? ዕውር ዕውርን እየመራው ገደል እንጂ ገነት አይጠበቅም።

yiheyisaemro@gmail.com

( ክፍል 3 ሳምንት ይቀጥላል )

## የደቡብ አፍሪካው የነጻነት ታጋይ እና የቀድሞ ፕሬዝዳንት ኔልሰን ማንዴላ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ማዲባ ከ27 ዓመታት እስር በኋላ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1994 የመጀመሪያው ጥቁር የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ለመሆን በቅተዋል፡፡ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1999 ደግሞ በፈቃዳቸዉ በቃኝ በማለት ስልጣን “በቃኝ” በማለት የሚተዉ ነገር መሆኑን ስልጣን ላይ ለመቆየት ባለጋራዎቻቸዉን ለሚገድሉና ለሚያስሩ የዓለም በተለይ የአፍሪካ መሪዎች ትምህርት አስተምረዋል። ማዲባ በሃገሩ ደቡብ አፍሪካ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ እንዲሁም በመላው ዓለም እጅክ ከፍተኛ ክብር ያለው የነጻነት ታጋይ ነው፡፡

ኔልሰን ማዴላ ሎን ዎክ ቶክ ፍሪደም በተሰኘው እና የራሱን ታሪክ በሚያወሳው መጽሃፉ ኢትዮጵያን በተመለከተ የሚከተለውን ጽፏል ኢትዮጵያ ምንግዜም በልቤ ልዩ ቦታ አላት፤ ለእኔ ኢትዮጵያን መጎብኘት አሜሪካን፣ እንግሊዝን እና ፈረንሳይን በአንድ ላይ ከመጎብኘት የበለጠ ያስደስተኛል፤ አፍሪካዊ ያደረገኝን ምንነት ለመመርመር የዘሬን ስረ መሰረት የጎበኘሁ ያህል ነው የሚሰማኝ፡፡

## የግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል መጠናከር ወያኔን የቀን ቅዠት . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ወይም በማጭበርበር ከሀገርና ከሕዝብ በመዝረፍ ያጠራቀሙትን ከፍተኛ ሃብት በሰላም ለመብላት ሲመኙ የኖሩት የወያኔ ቁንጮዎች፤ ይህን ሃሳባቸውን የሚረብሽና ቀንም ሌትም ሰላም የሚነሳ ሕዝባዊ ሃይል መፈጠሩ ርፍት እንደነሳቸው በሚወስዱት ርምጃ ገሃድ እየሆነ ነው። የህዝባዊ ሃይሉ የትግል ቦታ ድረስ አስርገው በማስገባት ግድያ ሊፈጽሙ ያሰቡት ሳይሳካ መቅረት እጅጉን ተስፋ ያስቆረጣቸው ሲሆን አሁን ደግሞ ከግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይልና ከግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ባለሌላ ማዕረግ አማራና ኦሮሞ ወታደሮችና ባለስልጣናት ከስራ ቦታቸው እንደሚቀነሱ ታውቋል።

ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ፋሽስት ወያኔ ሊወስደው ነው የሚባለው ቅነሳ ስጋቱን ያባብሰው እንደሁ እንጅ አያቀለውም ያላሉ። እንደምክንያት ሲጠቅሱም ከዚህ በፊት የተለያዩ ችግሮችን በማስታከክና አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማመካኘት የተለያዩ እስሮችንና የስራ ቅነሳዎችን ቢያደርግም የሕዝባችንን ምሬት አናረው እንጅ አላበረደውም። ስለሆነም አሁንም ፋሽስት ወያኔ ሕዝብን ለማዳመጥ ወደ ሕዝብ ጥያቄዎች እስካልተመለሰ ድረስ የፈለገውን አይነት ርምጃ ቢወስድ ሕዝባችን ከያዘው የዲሞክራሲ ጥያቄ ፈቀቅ ሊያደርገው አይችልም ይላሉ።